## ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሲያጋጥሞት እና ተከስቶ ሲመለከቱ ለማን ሪፖርት ያደርጋሉ?

ፆታን መሰረት ያደረገ  ጥቃት ሲፈፀም ጥቃቱ የደረሰበት ሰው ወይም ጥቃቱን ሲፈፀም ያየ ሰው በአቅራቢያው ላለ የህግ ወይንም የፍትህ አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።ከዚህም በተጨማሪ በሚከተሉት ቁጥሮች በመደወል ማሳወቅ ይችላሉ።

**6388** አለኝታ ድፃቾሁ ይሰማል! (ሴታዊት)
**7711** የህግ ድጋፍ እና ማማከር አገልግሎት ለማግኘት(የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር)
የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት
ስልክ፡- **+251118217758/59**
የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማህበር
**+251-9-11-76-80-52**
**+251-1-16-67-22-90**

### ለተጨማሪ መረጃ


አድራሻ፡
የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (ኢ.ሴ.ማ.ቅ)
ስልክ፡-**+251118217758/59**
ፖስታ፡- **19357**
ማህበራዊ ሚዲያ፡-
www.facebook.com/newa.ethiopia
www.twitter.com/cf-newa
www.newaethiopia.org




NEWA

AMBASSADE DE FRANCE EN ÉTHIOPIE ET AUPRÈS DE L'UNION AFRICAINE
*Liberté Égalité Fraternité*

GBVC-ETH

# “ሰላም ይስፈኝ! ፆታዊ ጥቃት ይቁም”

## የ16ቱ የንቅናቄ ቀናት -ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ላይ



### የ16 ቀናት በፆታዊ ንቅናቄ ምንድን ነው?

የ16 ቀናት በፆታዊ ንቅናቄ እንደ አውሮፓዉያን አቆጣጠር ከ1991 ጀምሮ በአለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን ጥቃት ለማስቀረት በሚደረገው እንቅስቃሴ የማስተባበር ተግባር መታሰቢያነት ሲውል ቆይቷል። በአለም አቀፍ ደረጃ ከኖቬምበር 25 (አለም አቀፍ የሴቶች ጥቃት መከላከል ቀን) ጀምሮ እስከ ዲሴምበር 10 (የሰብአዊ መብት ቀን) ድረስ ባሉት የ16 ቀናት የንቅናቄ ዘመቻ የሚካሄድ ሲሆን ሁለቱ ቀናት የተመረጡበት ዋና ምክንያትም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቀረት እና የሰብአዊ መብት እሴቶች ቁርኝትን አፅኦት ለመስጠት እንዲሁም የሴቶች ጥቃት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥሰት መሆኑን ለማመላከት ነው።

### ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት- የኢትዮጵያ ቡድን

በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት መሪነት የሚሰባሰበው ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት -የኢትዮጵያ ቡድን ከ2006 ጀምሮ በሃገር አቀፍ ደረጃ የፆታዊ ጥቃትን ለመቀነስ ብሎም ለማቆም የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ይህ ቡድን በ16 ቀናቱ የሚከበሩ ቀናትን በጋራ በማክበር፣ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት፣ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የግፊት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ የምክክር እና የውይይት መድረኮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ በማዘጋጀት እና ጥቃቱ የደረሰባቸውን ወገኖች ለማሰብ የሚረዱ የሻማ ማብራትን ጨምሮ ሌሎች ተግባራትን በማከናዎን በአንድነት ዘልቋል። ይህ ቡድን በዚህ አመትም ሰፋፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የግፊት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል።



## የዘመቻ በፆታዊ ጥቃት- የኢትዮጵያ ቡድን አባላት



- የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት
- የኢትዮጵያ ሴት አካል ጉዳተኞ ብሄራዊ ማህበር
- የሴቶች ይችላሉ ማህበር
- አዲስ አበባ ሴቶች ማህበር
- የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር
- ፋሚሊ ሰርቪስ አሶሴሽን
- መጀጀጉዋ ሎካ የሴቶች ልማት ማህበር
- ሲቄ የሴቶች ልማት ማህበር
- የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽ
- ሳራ ፍትህ ከሁሉም
- ሴታዊት
- የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማኅበር
- National Young Women's' charity Organization (NYWCO)
- Unwomen
- Actionaid

የዘመቻ በፆታዊ ጥቃት የኢትዮጵያ ቡድን አባላት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሲሆኑ ከተለያዩ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ተቋማት እንዲሁም የሲቪል ማህበራት ጋር በመተባበር የ16ቱን ቀናት ንቅናቄ ያካሂዳሉ።

## በአስራ ስድስት ቀናት የንቅናቄ ዘመቻ ላይ የሚታሰቡ ቀናት

- ህዳር 16 ዓለም አቀፍ የነጭ ሪቫነ ቀን
- ህዳር 30 ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከላካዮች ቀን
- ህዳር 22 ዓለም አቀፍ የኤድስ ቀን
- ህዳር 24 ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን
- ህዳር 27 ዓለም አቀፍ የጥቃት ሰለባዎች ቀን
- ታህሳስ 1 ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ቀን

## የ16 ቀናት ንቅናቄ ትኩረት ምንድን ነው?

የ16 ቀናት ንቅናቄ በዋናነት ተኩረቱን ያደረገው ከላይ በተዘረዘሩት ቀናት ላይ ሲሆን ከእነዚህም በዋናነት፡- ፆታዊ ጥቃትን በመቃወም ላይ ትኩረት ያደረጉት እነዚህ የእንቅስቃሴ ቀናት በዘርፉ የሚሰሩ አካላትን በማሰባሰብ እና ልምዶችን በመለዋወጥ የተገኙ ውጤቶችን ያጋጠሙ ችግሮችን ወደኋላ መለስ ብለው የሚመለከቱበት፤ ከዚያም አልፎ ውሳኔ ሰጪው መንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ለጉዳዩ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጡ የሚጠየቁበትና ድምፃቸውን የበለጠ እንዲሰማ የሚሰሩበት ወቅት ነው።




የ16ቱ ቀን ዘመቻ በአለም አቀፍ ደረጃ ፆታዊ ጥቃቶችን ለማስቀረት ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ማደራጃ ስልት በመሆን ያገለግላል። ምንም እንኳን በተለያዩ አካላት የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ቢሆኑም እና የፆታዊ ጥቃትን ለመቀነስ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ያሉ ቢሆንም አሁንም በተለያየ ሁኔታ እና ቦታዎች የፆታዊ ጥቃት በሰፊ ሁኔታ እየተፈፀመ እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ።

በመሆኑም በዚህ አመት በዓለም አቀፍ ደረጃ የ16ቱን ቀናት ንቅናቄ **"ORANGE THE WORLD: END VIOLENCE AGAINST WOMEN NOW"** በሚል መሪ ሃሳብ ይከበራል። ይህም በአንድነት የመቆም ምልክት የሆነውን ብርቱካናማ ቀለም በማስቀደም ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አሁን ዛሬ ይቁም የሚለውን ሃሳብ ያነገበ ነው።በሃገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ **"ሰላም ይስፈን! ፆታዊ ጥቃት ይቁም!"** በሚል መሪ ሃሳብ እንዲከበር በንቅናቄ ቡድኑ ተመርጧል።

ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት- ኢትዮጵያ ቡድን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እና መሪ ሃሳብ በእጅጉ ይደግፋል። ከዚህም በተጨማሪ በሃገራችን ያለውን አለመረጋጋት እና ግጭት በዚህም ሳቢያ በሴቶች ላይ እየደረሱ ያሉ ፆታዊ ጥቃቶችን ታሳቢ በማድረግ **"ሰላም ይስፈን! ጥቃት ይቁም!"** በሚል መሪ ሃሳብ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ያከብራል።

ይህ መሪ ሃሳብ የተመረጠበት ዋና ምክንያት በሃገራችን በተለያየ ጊዜ እና አካባቢዎች እየተቀሰቀሱ ያሉ ግጭቶች፣ አለመረጋጋት ብሎም ጦርነት ቀዳሚ ገፈት ቀማሽ ሴቶች እና ህፃናት ሴቶች በመሆናቸው ግጭቶችን መፍታት እና ዘላቂ ሰላም ትልቅ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች መሆናቸውን በማመን እንዲሁም በግጭት ወቅት የፆታዊ ጥቃት ተግባራት በቂ የህግ ምላሽ እንዳያገኙ ስለሚያደርግ ነው።ከዚህም ሌላ በተለያየ ሁኔታ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶችን ሁሉም የሚመለከተው አካል እና ማህበረሰቡ በጋራ ሆኖ በመዋጋት ፆታዊ ጥቃትን ያስቆም ዘንድ ጥሪ ለማድረግ ነው። ግጭቶች እና አለመረጋጋቶች በአካባቢያዊ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚያደርሱት ውድመት የሴቶችን የስራ ጫና እንዲባባሱ ከማድረጋቸው ጀምሮ፣ ሴቶች ላይ የፆታዊ ጥቃት ማድረስ እንደ ግጭት ማሸነፊያ መሳሪያ ማየት እንዲሁም በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲፈናቀሉ  እና የጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ ማድረግ በግጭት ወቅት ከሚከሰቱ ችግሮች ዋነኞቹ መሆናቸውን ለመገንዘብ አያዳግትም።

በዚህ አመት ፆታን መሰረት አድርጎ የሚፈፀምን ጥቃት ዘመቻ መሪ ሃሳቡን በማጉላትና የቅስቀሳ ስራዎችን በመስራት ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ፣ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጥቃትን ለማስቀረት አላማ አስቀምጦ ይተገብራል።

